የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 33
ADDIS ABABA 14th May, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፩/፪ሺ፮ ዓ.ም

ግብርናን ዘመናዊ ለማድረግ የሚውል ብድር ከፖላንድ ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...............ገጽ ፯ሺ፫፻፹፮

**CONTENTS**

**Proclamatoin No. 831/2014**

Government of the Republic of Poland Credit Agreement for Financing Modernization of Agricalture Ratification Proclamation ............................ Page 7386

አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፩/ ፪ሺ፮

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ግብርናን ዘመናዊ ለማድረግ ለሚያግዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚውል ፶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃምሳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATOIN No. 831/2014**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF POLAND**

WHEREAS, an Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Poland stipulating that the Government of the Republic of Poland provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amounting to 50,000,000 USD (fifty million United States Dollars) for financing the value of contracts for delivery of goods and services that help in the modernization of agriculture was signed in Addis Ababa on the 25th day of February, 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 27th day of March, 2014;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ግብርናን ዘመናዊ ለማድረግ የሚውል ብድር ከፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፩/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃምሳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Government of the Republic of Poland Credit Agreement for the Financing Modernization of Agriculture Ratificaiton Proclamation No. 831/2014".

2. **Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement signed in Addis Ababa on the 25th day of February, 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Poland is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 50,000,000 USD (fifty million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of May, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**